# ሥህተቶችን ሳንደግም የተሻለች ኢትዮጵያን ወደ መገንባት

ገለታው ዘለቀ

በሚመጣው ህዳር ወር ላይ የኢትዮጵያ ልጆች የኦሮሞ ብሄር ለሂቃን ተሰብስበው በከፍተኛ ጉዳዮች ላይ ይመክራሉ ሲባል ምክክሩን ወድጄው በስብሰባው ላይ ቢነሳ ጥሩ ነበር ብየ ባሰብኩት ላይ ለመወያየት ነው አነሳሴ። የውይይቱ አሳብ ለሁሉ ኢትዮጵያዊ ሁሉ ነው በርግጥ። እነዚህ የኦሮሞ ወገኖቼ ከዚህ ስብሰባ በሁዋላ የሚያወጡት የአቋም መግለጫ የኢትዮጵያን ማህበረ ፓለቲካ ለመለወጥ ትልቅ ድርሻ ያለው የትብብር፣ የአንድነት አሳብ እንደሚሆን አምናለሁ።

በአሁኑ ሠዓት ኢትዮጵያችን በከፍተኛ ህዝባዊ ንቅናቄ እየተናጠች ነው። ምን አልባትም ይህ ዓይነቱ ህዝብ መራሽ የሆነ ሰፊ ትግል በታሪካችን አልታየም። የህዝባዊ አመፁ በከፍተኛ ሁኔታ እየገፋ ባለበት በአሁኑ ወቅት የፓለቲካ ሃይላት ሲቪክ ድርጅቶችና የሃይማኖትና የባህል መሪዎች ሁሉ ሁለት ትላልቅ የምክክር አጀንዳዎች ከፊታቸው ተደቅነዋል። በተናጠልም በጋራም በነዚህ ጉዳዮች ላይ መወያየት አለብን። አንደኛው ወቅታዊ ጉዳይ ይህ የህዝብ ትግል እንዴት ነው የሚቋጨው? እንዴት ነው የሚያልቀው? የሚለው አስቸኳይ ጉዳይ ሲሆን ሁለተኛው ደግሞ

በሽግግሩ ጊዜ ሊሰሩ የሚገባቸው ስራዎች ላይና የሽግግሩ ጊዜ ምን መምሰል እንዳለበት በመምከሩ ላይ ያተኮረ ነው።

በነዚህ ሁለት ነጥቦች ላይ ኢትዮጵያውያን ባሉን አጋጣሚዎች ብንወያይ መልካም ነው። ከፍ ሲል እንዳልኩት ትግሉ ሰፊና አስደናቂ ሲሆን በአብዛኛው አካባቢያዊ ጥያቄን እያሳየ አጠቃላይ የስርአት ለውጥን ፈላጊ ሆኖ ይታያል። የትግሉን ባህርይ ስናይ በኦሮምያ አካባቢ በአመዛኙ ሰላማዊ ህዝባዊ አመፅ ሲሆን በአማራ አካባቢ ደግሞ በሰላምም በትጥቅም የመታገል ባርይ አለው። በአሁኑ ሰአት ትግሉን የደቡብ ህዝብም የተቀላቀለው ሲሆን ከፍተኛ ደረጃ ላይ ደርሷል። እንግዲህ ታዲያ ይህ ትግል ሄዶ ሄዶ በምን መንገድ ይጠናቀቃል? እንዴት ነው የሚያልቀው? ህዝብ የትግሉን ድል እንዴት አድርጎ ነው የሚያየው የሚለውን ማጥናት ተገቢ ነው። ይህን እንድንጠይቅ የሚያደርገን የትግሉ ባህርይ ነው። ባለቤቱና የሚመራው ህዝቡ በመሆኑ (ይህንን ጽሁፍ ሳዘጋጅ አንዳንድ ሃይሎች እኛ ነን ትግሉን ያቀጣጠልነው ቢሉም) እንዴት ይህ ትግል ወጥ የሆነ አመራር አግኝቶ መንግስት ይለውጣል? የሚል ጥያቄ ያስነሳል። መቼም የህዝቡ ትግል ሲያይል ሊከሰት ይችላል ተብሎ ከሚጠበቀው መሃል አንዱ መፈንቅለ መንግስት ነበር። ነገር ግን በኢትዮጵያ ሁኔታ ይህ ነገር የሚከሰትበትን እድል ማየት ተገቢ ነው። ማን በማንስ ላይ ነው መፈንቅለ መንግስት የሚያደርገው። ተደረገ ቢባልስ ራሱ ሰራዊቱ ህወሃትን አይደለም ወይ የሚጠብቀው? ምን ለውጥ ይመጣል? የሚል ነው። ሌላው የዚህ የህዝብ ተቃውሞ ግፊት መንግስትን ወደ ብሄራዊ እርቅና መግባባት የመወሰድ ሃይል ነበረው። ይሁን እንጂ መንግስት ለዚህ

ልቡ ተሰብሯል ወይ? ስንል አይመስልም። እስካሁን ምልክቶች አይታዩም። በብሄራዊ እርቅ ዙሪያ የሚሰሩ አሉና እስቲ እነሱ እየገፉ ይሂዱና ለውጥ ካለ እናያለን። እነዚህ ጉዳዮች ካልሰሩ ታዲያ ይህ የህዝብ አመጽ እንዴት ነው ድሉን የሚጨብጠው? ብለን እንጠይቃለን። መቼም መንግስት ህዝቡ በየከተማው አምፆብኛልና ጥይት የለኝም ብሎ ወታደር አሰናብቶ የአራት ኪሎን ቤተመንግስት ነቅሎ አይሄድም። በመሆኑም ይህ የህዝብ ትግል በድል እንዲጠናቀቅ የግድ የታጠቀ ሃይል ወጥ የሆነ እዝ ያለውን ሃይል ይሻል። ይህ የታጠቀ ሃይል ህዝብ ያደከመውን መንግስት በትጥቅ ጥሎ የሚመካበትን ሃይል በቁጥጥር ስር አውሎ ሲያበቃ ነው ይህ ትግል የሚቋጨው። ይህ የታጠቀ ሃይል የሚያስፈልገው ቋፍ ላይ ያለውን መንግስት ለመናድ ብቻ ሳይሆን የሽግግር ጊዜውን ለማድረግ በመላ ሃገሪቱ የሰላም ማስከበር አገልግሎት መስጠት ስላለበት ነው። በርግጥ ይህ ሃይል ሲያሸንፍ አሁን ያለውን መከላከያና ፓሊስ በሙሉ ይበትናል ሳይሆን እነዚህን ሃይሎች በአዲስ መንፈስ አንፆ መሄድ ይኖርበታል። ትግሉ ሊቋጭ የሚችለው እንግዲህ በታጠቀና የህዝቡን ጥያቄ ባነገበ ብሄራዊ ሃይል በመሆኑ አሁን በየአካባቢው ያለውን ሃይል ወደ ወጥ እዝ በማሰባሰብ የመጨረሻውን ትግል ማድረግ ያሻልና የመጨረሻውን ትግል ለመምራት ዝግጁ ነን ሃይል አለን የሚሉ ሃይሎች ይህን ጉዳይ ማሰብ ይኖርባቸዋል። የአካባቢ ትግሎች በበቂ የተደረጉ ሲሆን አሁን ህብረብሄራዊ የሆነ ሃይል ባስቸኳይ መውጣት አለበት። በመሆኑም የታጠቁ ሃይሎች ወደ ህብረት መጥተው ህብረቱን ለህዝብ መግለፅ ይጠበቅባቸዋል። በተግባርም የኦፐሬሽን ስራዎች መጀመር አለባቸው። የኦሮሞ ለሂቃንም ሆኑ የአማራ ወዘተ. በጋራ በመነጋገር የህዝቡን ትግል በድል እንዲቋጭ እዚያም

እዚያም የተበታተነውን ሃይል በአንድ ወጥ እዝ ስር አድርገው ትግሉን መምራት ካልቻሉ ኦሮሞ ለብቻው አማራ ለብቻው ወዘተ ሰራዊት ለመገንባት ከጣሩ ይህ ትግል ወደ ብዙ አቅጣጫ የመውደቅ እድል ይኖረዋል። የአንድ ብሄር የታጠቀ ሃይል ድል ቢያደርግም እንኳን ለኢትዮጵያ ጥሩ አይሆንም። ህወሃት 25 ዓመት ሙሉ የሚለው አብላጫ ታግያለሁና አብላጫ ይገባኛል አይነት ነው። በመሆኑም በተናጠል የነበረው ትግል አሁን ይጠናቀቅ ዘንድ ህብረትን ፈልጓል። ትግሉ ብሄራዊ ንቅናቄን የሚሻበት የመጨረሻ ምእራፍ ላይ ነውና መነጋገር ያስፈልጋል ነው የምላችሁ።

ሁለተኛው ወቅታዊ ጥያቄ ደግሞ ያለፈ ስህተት እንዳይደገም የሽግግር ጊዜው ምን መምሰል አለበት? በዚህ የሽግግር ጊዜ ምን ልንሰራበት ነው? የሚለው ጥያቄ ነው።

ኢትዮጵያችን ከዘውዳዊ አገዛዝ ወደ ዘመናዊ አስተዳደር መሻገር ሲያምራት የሽግግር ጊዜን የፅሞና ጊዜ አድርጋ አልወሰደችም። ወታደር ስልጣኑን ነጥቆ ወስዶ ለስሙ የሽግግር ጊዜ ቢልም በተግባር ግን የሽግግር ጊዜ አላየንም። ራሳቸው መንግስቱ “በውኑ ደርግ አለን” ብለው የኢትዮጵያን ህዝብ ቢጠይቁት እስካሁን በዚህ ጥያቄ ይሳለቃል። በህወሃት ኢህአዴግ ጊዜም እንዲሁ የሽግግር ጊዜ ሲጠበቅ ሰፊ ማህበረሰብ ያገለለ የሽግግር ጊዜ የማይባል አሳልፈን ቀረን። የኢትዮጵያን ህዝብ መሰረታዊ ጥያቄ በሚገባ የምናጤንበት ጊዜ ሳይኖረን ቀረ። ለሶስተኛ ጊዜ ተመሳሳይ ችግር ውስጥ እንዳንገባ በዚህኛው ለውጥ ጊዜ ስለ ሽግግር ዛሬ ላይ ሆነን ማሰብ አለብን።

በተለይ የኢትዮጵያ ፓለቲካ አሰላለፍ ወዲያና ወዲህ በሆነበት በዚህ ልዩ ጊዜ የሽግግር ጊዜ የጽሞናና የእቅድ ጊዜ የግድ ያስፈልገናል። በዚህ የሽግግር ጊዜ የሚያስፈልገው ዋና ነገር ምንድን ነው? ካልን የስምምነት አሳብ ነው። ይህ አሳብ ኢትዮጵያውያንን ወደ አንድ የተሻለ አዲስ ኪዳን የሚወስዳቸው መሆን አለበት። በዚህ የሽግግር ሰአት ኢትዮጵያውያን ባህላዊ ኢኮኖሚያዊ ፓለቲካዊና ማህበራዊ ጉዳዮቻቸውን እንዴት አድርገው ማስተዳደር እንደሚገባቸው በዘላቂ ጉዳይ ላይ አቋም የሚይዙበት ሰአት ነው። ኢትዮጵያውያን ብዙህ ሆነው ግን ደግሞ አንድ አገር እንዲኖራቸው ይሻሉ። ይህ ማለት እንግዲህ ይህ የፈለጉት አንድነት የሚጠይቃቸውን የመስዋእት ጥያቄ አይፈሩም ማለት ነው። ስለሆነም የስምምነቱ አጀንዳ መሆን ያለበት እንዴት አድርግን አንድ ትልቅ አገራዊ የፓለቲካ ጠገግ እንፍጠር የሚል እና በሌላ በኩል ደግሞ ባህላዊ እኩልነትን የምናሳይበትን ሲስተምና ጠገግ መፍጠር ነው። የስምምነቱ አሳብ ይህን ያዘለ ሆኖ ነገር ግን መስዋእቱን የሚያቀርበውና አሳቡን የሚያፀድቀው ህዝብ፣ ዜጎች ሁሉ መሆን አለባቸው። በዚህ በሽግግር ወቅት ሊነሳ የሚገባው አንድ ጉልህ ጉዳይ የአንድነት ትርጉም ነው። የአንድነት መገለጫዎች ምን ምን እንደሆኑ መታወቅና ስምምነት መያዝ አለበት። ይህ ጉዳይ የፓለቲካ ዶክትሪን ሳይሆን ዘመን ተሻጋሪ የሆነ መሰረታዊ የሆነ ሃገርን እንደገና የማነፅ ጉዳይ ነው።

እንደሰማነው የኦሮሞ ብሄር ተወላጆች የኦሮሞን ህዝብ ህልም የሚገልፅና ኦሮሞ ምን አይነት አገር በአዲሲቷ ኢትዮጵያ እንደሚፈልግ ሊወያዩ ነው። መወያየት አሳብ ማምጣት ደግ ነገር

ነው። ሌሎች ቡድኖችም እንዲሁ በየቡድኑ ምክክር እያሰቡ እንደሆነ አላውቅም። ነገር ግን ያም አለ ይህ ለአዲሲቱ ኢትዮጵያ የሚያስፈልገውን መስዋእቶች ሁሉ እንዳንረሳ ያስፈልጋል። የኦሮሞ ህዝብ ጥያቄ የፍትህ የነፃነት የእኩልነት ጥያቄ በመሆኑ ይህንን የሚያስከብር ስርአት አብሮ መምከር እንጂ የኢትዮጵያን መስዋእቶች የሚበላ ወይም የሚቀራመት መሆን የለበትም። አማራ፣ ሲዳማ ወዘተ ለየብቻ ስለመጪው ጊዜ ስለሽግግር ጊዜው የስምምነት አሳቦች መወያየት ሲያምራቸው ለኢትዮጵያና ኢትዮጵያዊነት የሚሆነውን መስዋእት ካላሰቡ የተሻለች አገር አንገነባም። የሽግግሩ ጊዜ ሊያነሳው የሚገባው የስምምነት አሳብ አንድ የኢኮኖሚና የፓለቲካ ማህበረሰብ መፍጠርና ባህላዊ ማንነትን ራሱን በቻለ ነፃ አስተዳደርና የባህል ፌደሬሽን ማስተዳደር ነው። በኢትዮጵያ ውስጥ የብሄር ትግል አድራሽ መሆን ይኖርበታል። እስከ ሽግግሩ ጊዜ ቀይቶ ከዚያ በሁዋላ ሊሟሟ ይገባል። የብሄር ፓለተካንም አንድነትንም ይዘን ብሄራዊ ምርጫ አድርገን ወደተሻለች ኢትዮጵያ መሻገር አንችልም።መወሰን አለብን። በአዲሲቱ ኢትዮጵያም የብሄር ፓለቲካን ካልጎተትን ካልን ሃገሪቱ ብዙ ግልፅነት በሚጎድላቸው የባህል የአኮኖሚ የማህበራዊና የፓለቲካ ስርአት ውስጥ መውደቋ ይቀጥላል። ግልፅ ያልሆነ ስምምነት ይዘን ያልቆረጠና የሰሰተ ስምምነት ይዘን አዲስ ስርአት መመስረት አንችልም። ይህን የምንልበት ብዙ ምክንያቶች አሉ። ዘውግ ለአዲሲቱ ኢትዮጵያ የስልጣን ምንጭ ይሁን የሚሉ ሃይሎች ሊመልሷቸው ከሚገቡ ጥያቄዎች መሃል

1. የብሄር ፓለቲካ በኢትዮጵያ ብሄሮች፣ በኦሮሞ፣ በአማራ፣ በትግሬ ወዘተ. ባህልና እምነት እሴቶች ውስጥ አለ ወይ? በነዚህ ብሄሮች እሴቶች ልብና መንፈስ ውስጥ ይገኛል ወይ? ብለን ልንመረምረው ይገባል። የኢትዮጵያ ብሄሮች በሃይማኖቶቻቸውም ሆነ በባህሎቻቸው እኔ....እኔ..... እኔ ....የሚል ነገር አያበረታቱም። አብረው በሚኖሩበት አገር ውስጥ የኔ....የኔ...የኔ....የሚል እሴት የላቸውም።

ለምሳሌ የኦሮሞን የገዳ ስርአትና ሌሎች ባህሎቹን ብናይ አንድ ከኦሮሞ ብሄር ውጭ ያለ ሰው ወደ ኦሮሞ ማህበረሰብ ከሄደና አብሮ ከኖረ እንደ ኦሮሞ ነው የሚታየው። የኦሮሞ ማህበረሰብ ባህል ይህንን ሰው እንዲለይ አይፈልግም። ከገዳ ስርኣትና ከአጠቃላይ የኦሮሞ ባህል መርሆዎች የሚቀዳው የፓለቲካ እምነት የብሄር ፓለቲካ ሳይሆን ሁሉን አቀፍ የሆነ በዜግነት ላይ የተመሰረተ ፓለቲካ ነው። የኦሮሞ ህዝብ መሪዎች ነን የሚሉ ሃይሎች በዘውግ ላይ የሚመሰረት ፓለቲካ የሚያራምዱ ከሆነ የኦሮሞን ባህል እሴቶች እየሰበሩ መሆናቸውን ማጤን አለባቸው። የገዳ ሥርኣት የኦሮሞ ባህል ብቻ ሳይሆን ጌዲኦም ይህን ባህል ይከተላል። የጌዲኦ ህዝብም እንዲሁ ለባህሉ እሴቶች ይጠነቀቃል። በአጠቃላይ የኢትዮጵያ ብሄሮች አብረው በአንድ ገበታ ይበላሉ። አንተ ትብስ .........አንተ ትብስ..........ይባባላሉ። አይሰስቱም። ይሉኝታ አላቸው። የብሄር ፓለቲካን እሴቶች ስናይ ደግሞ ከራስ በላይ ነፋስ አይነት ልብ አለው። ራስን በራስ.......የራስን እድል በራስ.....የራስ ባህል.........የራስ መሬት .....ራስ...ራስ..ራስ....ነው ጨዋታው። የብሄር ፓለቲካ ከሶሻሊስት አብዮት የተቀዳ

የእኛን ባህልና ሃይማኖት የሚፃረር በመሆኑ ነው በህብረተሰቡ ዘንድ ምስቅልቅልን እንዲያመጣ ያደረገው። ይህን የሚሸከም ባህላዊም ሃይማኖታዊም መሰረት የለንም። በመሆኑም ይሄን የሃገራችንን ባህልና ሃይማኖት የሰበረ ስስታም የፓለቲካ ዶክትሪን  ልንከተለው አይገባም። ራስ....ራስ...ራስ.....ከሚለው ወጥተን እኛ...እኛ...እኛ .......ወደሚል የፓለቲካ አስተሳሰብ ስንገባ ነው የአማራን ወይም የኦሮሞን ወይም የሌሎችን ብሄሮች እሴቶች የምናከብረው።

2. የዴሞክራሲ ጉዳይ። ዘውግን ለአደሲቷ ኢትዮጵያ የስልጣን ምንጭ ማድረግ ከፈለግን የዴሞክራሲ መርሆዎችን ልንረማመድባቸው ነው። ምርጫን የዜግነት መብትን ሁሉ ይጋፋብናል። ስለዚህ እንምረጥ። ዴሞክራሲን ከነሙሉ ክብሩ ለአዲሲቱ ኢትዮጵያ ከተመኘን ከዘውግ ፓለቲካ መላቀቅ አለብን።
3. የብሄር ፓለቲካ ግብ ምንድን ነው? ብለን እንጠይቅ። ኢትዮጵያን የሚያክል ጠገግ እንደ ኮንትራት አድርገን ብሄርን ዘላለማዊ ጠገግ አድርገን  አገር መመስረት ካማረን ከስረናል። የብሄር ፓለቲካ ችግር ይህ ነው። አካባቢያዊ ማንነትን እያጎላ ብሄራዊ ማንነትን ያኮስስና አገርን ያናጋል። ዘላቂ ግብም የለውም።
4. የአባቶች ደምና አጥንት ጉዳይ። ኦሮሞው ሲዋጋ የኖረው አሁን ወያኔ ለፈጠረው የኦሮምያ ካርታ አይደለም። ትግራይ ሄዶ ነው የሞተው። አማራው ጉራጌው ትግሬው ሁሉም ዘብ ሆኖ ሲጠብቅ የኖረው ኢትዮጵያን ነውና የአባቶች ህብረት በዚህ ትውልድ መከበር አለበት። በደምና አጥንታቸው ላይ የምንረማመድ ትውልድ እንዳንሆን።

5. የብሄር ፓለቲካ ህዝባዊ ጥያቄ አለው ወይ? ብለን እንጠይቅ። ከጥቂት ሰዎች በላይ ህዝባዊ መሰረት የለውም። ይህንን ማጥናት ይቻላል። የሁሉም ህዝብ ጥያቄ አንድ አይነት ነው። ፍትህ ነፃነት።
   በርግጥ ነው ቡድንን ነጥሎ የሚያጠቃ ሲመጣ መመከት ተገቢ ነው ይሁን እንጂ በተረጋጋ መንግስት ጊዜ ዘውግ የፓለቲካ መሰላል እንዲሆን የሚሻ ኢትዮጵያዊ በጣም ጥቂት ነው።
6. የብሄር ፓለቲካ አሁን ካለችው አለም ጋር ይሄዳል ወይ? ይህን ጥያቄ መመለስ ተገቢ ነው። አለም ወዴት እያመራች ነው? ሚለውን ወጣ ብሎ ማየት ያሻል። የብሄር ፓለቲካ ፊውቸር የለውም።
7. የጋራ ሃብትና የክልል ሃብት ላይ ትልቅ ንትርክ ያመጣል። አነሰም በዛም የጋራ ሃብቶች አሉን። እነዚህን ሃብቶች በኢትዮጵያዊነት ልንወርሳቸው ነው የሚገባው። የኔ የኔ ከመጣ ሁል ጊዜም ለአገሪቱ የግጭት ሃይል መቅበራችን ነው።
8. የማንነት እሽቅድምድም። ፓለቲካ ሁል ጊዜም የፍላጎት ማእከል(center of interest) አለው። ይህን ማእከል ለኢትዮጵያና ኢትዮጵያዊነት ሳንሰዋ ከቀረንና የዝንባሌና ፍላጎታችን ማእከል ብሄር ከሆነ በፍትህ ላይ ልንረማመድ እንችላለን። ፍትህ እኩልነት የሚታየን ከላይ ሆነን ስናይ ነው። ከላይ ከኢትዮጵያዊነት ላይ ሆነን.....። ከስር ከየብሄራችን የምናየው እይታ የሁሉን እኩልነት አያሳየንም። ከሁሉ በላይ ችግር ጎልቶ የሚታየን የኛ የምንለው ቡድን ይሆንና የሃገርን ለዛ ያጠፋብናል። ከዚህ የተነሳ እኔ መጀመሪያ ወላይታ ነኝ ሁለተኛ ቅብጥርሴ እያልን የማንነት እሽቅድምድም ውስጥ ይከተንና ፍትህን ምስጥ ሆኖ ይበላብናል።

9. ከብሄር ፓለቲካ ተምረን ተምረን ያፈራነው እውቀት ይህ ነው ወይ? ኢትዮጵያ ጥሟታል ወይ? ብለን መጠየቅ ተገቢ ነው። እንደ ኢትዮጵያውያን ስለዚህ ስለብሄር ፓለቲካ የተማረ የለምና እናስብበት። የብሄር ፓለቲካ በማህበረሰብ ህይወት ውስጥ ምን አይነት ሃይል (energy) እንደሚፈጥር ከሌላው አለም በተሻለ ተምረናልና እናስተውል።
10. የብሄር ፓለቲካ ፓሊሲዎችን ለማውጣት ምርምር ስናደርግ ልንቆጣጠራቸው የማንችላቸው ብዙ ተለዋዋጮች (variables) አሉት። ብዙ ጥያቄ ለማኝ የሆኑ ጉዳዮችን በውስጡ የያዘ ነው።
11. የብሄር ፓለቲካ ፍትህን ዴሞክራሲን ለማምጣት እንዴት ዋስትና ሆኖ ታየን? ሆሞ ጂኒየስ ሆኖ ጭቆና አለና። በአለም ላይ በብሄር ላይ እየተደራጁ ለስልጣን መሮጥ ለብሄሮች ቢጠቅም አለም ይህን ፍልስፍና በተከተለው። አለም እንደ ጦር የሚፈራውን ፓለቲካ ልንከተል አይገባም።
12. ቅይጡን ዜጋና ኢትዮጵያዊነትን እንደ ብሄር የወሰደውን ዜጋ ምን እናድርገው? ህወሃት ስታትስቲክስ ሲሰራ ብሄሮች ሲቆጠሩ ይህ ቅይጡ ቦታ የለውም። ገማቾች እንደሚሉት ይህ ቅይጥ ከሁለትና ሶስት ብሄር የተወለደው ዜጋ በቁጥሩ ከብዙ ብሄሮች ይበልጣል። ወደፊትም ቁጥሩ እየጨመረ ይሄዳል። የብሄር ፓለቲካ ሲመጣ ይህን ማህበረሰብ ለዘብተኛ ያደረገው ሲሆን ትልቁ ችግር ይህ ህዝብ በህሊናው የተሳለ ካርታ የለውም። ከቦታ ውጭ ይጥለዋል የብሄር ፓለቲካ። የፓለቲካና የዜግነት መብቱ በጣም ይሸራረፋል። በመሆኑም በዚህች አገር የብሄርን ፓለቲካ ለማስፈን የሚጥሩ ሃይሎች ይህን ሰፊ ማህበረሰብ ያስቡለት ዘንድ ይገባል።

ለማጠቃለል ያህል በፊዚክስ ትምህርት ውስጥ አንድ ጽንሰ ሃሳብ አለ ሲባል እንሰማለን። የስበትና የግፍትሪያ ህግ (laws of attraction and repulsion) ማለት ነው። ይህ ትምህርት የሚለው ግፍትሪያም ሆነ መሳሳብ የሚኖረው በዚያ በማግኔቲክ ፊልዱ ውስጥ ብቻ ነው። ከፊልዱ ውጭ ይህ ህግ አይሰራምና ግፍትሪያውም ስበቱም አይሰራም። ምን አልባት ይህ ተዛምዶ(Analogy)ምን ያህል አሳቤን እንደሚያሳይ ባላውቅም ነገር ግን የብሄር ፓለቲካ ሲስተም ዘርግተን ከዚያ በሁዋላ ችግር የለውም ለጋራው ቤታችን በገለልተኝነት አብረን እንሰራለን ማለት ከተፈጥሮ ህግ ጋር መታገል ነው። የሃገራችን ሰው ዘር ከልጓም ይስባል ይላል። በርግጥ በዘርና በደም ፓለቲካ ሲስተም ውስጥ ገብተን ብሄራዊ ተቋማት እንገነባለን ገለልተኝነት ያብባል ማለት ዘበት ነው። ከዚህ የብሄር ፓለቲካ የስበት ፊልድ ወይም የፓለቲካ መጫወቻ ሜዳ ወጥተን የተሻለች ለሁሉ የምትሆን ኢትዮጵያን መፍጠር የምንችለው የብሄር ፓለቲካ ሲስተም ውስጥ ሆነን ሳይሆን ከዚህ ሲስተም ወጥተን በመርህ ላይ ስንቆም ነው።

እዚህ ላይ አንድ መታየት የሚገባው እውነት አለ በርግጥ። ለራሴ የተማርኩት ነገር ቢኖር በብሄር መደራጀትን በተመለከተ በሁለት መንገድ አየዋለሁ። አንዱ ማንነትን እያነጣጠረ የሚያጠቃ ሃይል ሲመጣ በርግጥ ራስን መከላከል ያሻልና ቡድኖች ማንነታችንን አታጥፉ ብለው ሊደራጁና ለነፃነት ሊታገሉ ይችላሉ። ይህ ፍትሃዊ ነው። አንድ ቡድን

ተለይቶ ሲጠቃ ቢደራጅ አይደንቅም። ሁለተኛው መደራጀት በተረጋጋ አገር በመድብለ ፓርቲ ሥርአት ውስጥ በዘውግ ላይ ያተኮረ የብሄር ፓርቲ መመስረት ነው። ይህንን ነው አጥብቄ የምቃወመው። ስስታም፣ ሙሰኛ፣ አድልዎኛ የሆነ ልብ ያለው በመሆኑ ለሃገር አንድነት የማይጠቅም በመሆኑ ሁላችን ልናወግዘው ይገባል። ጎረቤት ኬንያን ጨምሮ ስዊዘርላንድን ጨምሮ በብዙ አገሮች ይህ ፓለቲካ ወንጀል የሚያስቀጣ ተደርጎ የሚወሰድ የፓለቲካ ዶክትሪን ነው። የዘር ፓለቲካ በህግ የሚያስቀጣ የሆነበት ምክንያት እነዚህ ሃገራት የዚህ ፓለቲካ ፍላጎት(motive) ወንጀል መሆኑ ስለገባቸው ነው።

በአጠቃላይ ኢትዮጵያን ወደተሻለ ስርአት ለመምራት በሽግግሩ ጊዜ ኢትዮጵያውያን አንድ ከፍ ያለ ዘመን ተሻጋሪ ስምምነት ሊያደርጉ የሚገባበት ጊዜ በመሆኑ ሃላፊነት ይሰማኛል የሚሉ ሃይላት ስምምነቱን እጅግ በሰከነ ሁኔታ ማድረግ ያሻል። አዲስ የሆነ ኪዳን ዜጎች ሁሉ ገብተው የምንቀጥልበት ሁኔታ እንዲፈጠር በስምምነት ላይ የተመሰረተ አንድነት እንድንፈጥር መጣር የሚጠበቅብን ወሳኝ ምእራፍ ላይ ነን። በመሆኑም አንደኛ ትግሉ ቶሎ እንዲጠናቀቅና ተፈላጊ ለውጥ እንዲመጣ ወጥ ንቅናቄ ማቋቋም ሁለተኛ የሽግግሩን ጊዜ  ኢትዮጵያ አዲስ ኪዳን የምትገባባት ጊዜ እንዲሆን ሁላችን እንትጋ። በቅርቡ ስብሰባ የጠራው የኦሮሞ ማህበረሰብም ሆነ ሌሎች በብሄር ላይ የተመሰረተ ድርጅት ያቆሙ ሃይሎች ሁሉ ደግመው እንዲወያዩበት የሚያስፈልገው ነገር ለኢትዮጵያ ምን መስዋእት እናድርግ? በሚለው ላይ ነው። አገር የሚመሰረትባቸውን አለባዎች ሁሉ ተቀራምተን ለህብረት

ዝግጁ ነን ማለት ባዶ ነገር ነው። ኢትዮጵያ የማትጨበጥ አይደለችም። የቡድኖችና የዜጎች መስዋእት ዋልታና ማገር ሆነውላት የምትኖር አገር ናት።

እግዚአብሔር የኢትዮጵያን ይባርክ።